# አጼ ኃይለ ሥላሴን ማድነቅ ጀመርሁ

ከአቶ ብርሃኑ ድንቄ ቄሳርና አብዮት ከሚለው መጽሐፍ የተገኘ ቦልቲሞር ሜሪላንድ

በዋሽኝንግተንና በጅዳ (ሳውድ አረቢያ) በዲፕሎማቲክ አገልግሎት 3 ዓመት ያህል ካሳልፍሁ በሁዋላ ለዘለቄታ አዲስ አበባ ተመልሼ የፖስታ ቴቴ ምክትል ሚኒስቴር ሆኜ ተሾምሁ፡፡ በዚይያን ጊዜ ሚኒስቴሩ ቢትወደድ መንገሻ ውቤ ነበሩ፡፡ አባታቸው የንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ ባል ስለነበሩ በልደታቸው የሚኮሩና ቤተ መንግስቱ የኛ ነው ባይ ናቸው፡፡ ለመጀመሪያ ከመስሪያ ቤታቸው በተገናኘሁዋቸው ጊዜ ይህን ስሜት ለኔ በማካፈል ከርሳቸው ጋር በሚኖረኝ ግንኙነት ለማስጠንቀቅ ሲሞክሩ አይቼ ከሶስት ዓመት የውጭ አገር ሰላማዊ ኑሮ በሁዋላ ያው የተለመደው ጭቅጭቅ እንደሚጠብቀኝ ተገነዘብሁ ፡፡

ቢትወደድ መንገሻ ብዙውን ጊዜ ታማሚ ስለ ነበሩ እንደሚኒስቴር ሆኖ የሚያዘው ታደሰ አብቼ የሚባለው ልዮ ጸሐፊያቸው ነበር፡፡ ሰለዚህ ከደንበኛ ደሞዙ በቀር ልዩ ዓበል ተመድቦለታል፡፡ነፃ የቴሌፎን አገልግሎት ከቤቱ ገብቶለታል፡፡ለመኪናው ቤንዚን ይሰጠዋል ፡ይህ ትክክል መስሎ ስለአልታየኝ ቢትወደድ ከመስሪያ ቤቱ ባልነበሩበት ጊዜ እንዲሰረዝ ትእዛዝ ፈርሜ አስተላለፍሁ።፡ ቢትወደድ ግን ለእረፍት ከሄዱበት ለዚሁ ሲሉ በፍጥነት ተመልሰው እኔ የሰጠሁትን ትእዛዝ የሚያፈርስ ደብዳቤ ብቻ ፈርመው ወደ እረፍታቸው ተመለሱ ፡፡ ስለዚህ የሚከተለውን ልጽፍላቸው ግድ ሆነብኝ፡፡

ክቡር ሆይ

ይህን መስሪያ ቤት ክቡርነትዎ እንዲያስተዳደሩ አላፊነት ሲሰጥዎ በነጋሪት ጋዜጣ ሰለሚኒስትሮች ሥልጣን የወጣውን ሕግ እንደሚያከብሩ በመተማመን መሆኑን አልጠራጠርም ፡፡የፖስታ ቴ.ቴ. ሚኒስቴር የመንግስት መስሪያ ቤት እንጂ የክብርነትዎ ማድቤት እንዳልሆነ ማስገንዘብ ያስፈልገኝ አይመስለኝም፡፡ልዩ ጸሀፊዎ ከተወሰነለት ደሞዝ በቀር ልዩ አበልና የቴሌፎን አገልግሎት እንዲሰጠው የበጀት ሥራ አይፈቅድም ፡፡ልዩ ፀሀፊው እርስዎ በሌሉበት ሚኒስቲር እንዲሆን ሕጉ አይፈቅድለትም፡፡ እርስዎ በሌሉበት ጊዜ ምክትል ሚኒስቴሩ አለ፡፡ ይህን ሁሉ አልፈው ልዩ ጸሐፊዎን የሚውክሉበት ምክንያት አይገባኝም፡፡የንጉሰ ነገስቱ መንግስት አስተዳደር አልተስማማዎት እንደሆነ የተሻለ መንገድ ስለሌለ ቢሰናበቱ መልካም ይመስለኛል፡፡ ከዚህ በላይ የተጻፈው ደብዳቤ ጠንካራ እንደሆነ ይሰማኛል

ግን የቢትወደድ አደራረግ ለኔ ጠንካራ ሁኖ ነው ያገኘሁት፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ አሠራራቸው ከሕግ ውጭ እንደነበር ሳያውቁት አይቀርም፡፡ ቀጥሎም የኔን ትዕዛዝ ከመፃረራቸው በፊት ጠርተው እንኩዋን ሊጠይቁኝ አልፈቀዱም፡፡ስለዚህ ለዘብ ያለ አቤቱታ እንደማይበግራቸው ተረድቼ ሆነ ብዬ ነው ያጠነከርኩት፡፡

በፖስታ ቴ.ቴሚኒስቴር በተጠባባቂነት ሰሰራ የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬጽን ቦርድ ሊቀ መንበር ሆኜ ቦርዱን መሰብሰብ ጀመርሁ፡፡ በዚያን ጊዜ የቴሌኮሚኒኬሺን  መስሪያ ቤት ስራውን ለማሻሻል ከዓለም ባንክ ከፍ ያለ ብድር ጠይቆ ነበር፡፡ ነገር ግን ገንዘቡ ከመፈቀዱ በፊት የአመቱን ገቢና ወጭ ሂሳብ እገልግሎት ተሰጥቶእቸው ያልከፈሉ ሰዎች እንዳለ የእዳቸውን መጠን የሚያሳይ ጠቅላላ ሬፖርት የቴሌኮሚኒኬሽን መስሪያ ቤት ለባንኩ እንዲልክ ማስታወሻ ደርሶት ነበር የስውዲን ተወላጅ የሆነው ዋና አስተዳዳሪው ሚስተር ሊንድኮስት ባዘጋጀው መልስ እንደተመለከትሁት ብዙ ሺህ ብር ያልተከፈለ እዳ ተገኘ። ምክንያቱን ብጠይቀው አብዛኛው ገንዘብየ ቴሌኮሚኒኬሺን ስለሰጠው የቴሌፎን አገልግሎት ንጉሳዊ ቤተ ሰቦችና መኩዋንንቶች ያልከፈሉት እዳ መሆኑን ገለጠልኝ ካቀረበው ዝርዝር ውስጥ የሚከተሉትን ስም ተመለከትሁ፡፡

ልዑል ሳህለ፣ ስላሴ ልዑል አልጋ ወራሽ፣ አስፋወሰን ህይለሥላሴ፣ ራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው፣ ራስ አበበ አረጋይ፣ ራስ ቢተወደድ አንዳርጌ፣ መሳይ አቶ መኮንን ሀብተ ወልድ ሌሎችም ብዙ አሉ፡፡

ሚስተር ሊንድኮስት ለ8 ወይም ለዘጠኝ ዓመት ከነዚህ ሰዎች አንድ ቤሳ እንኳዋን አልተቀበሉም፡፡ ምክንያቱን ብጠይቀው “ አንከፍለም ሲሉ ጊዜ ምን ማድረግ እችላለሁ ? ” አለኝ፡፡ “ሌሎቹ አንከፍልም ሲሉ ስልካቸውን ትቆርጣለህ ለምን እነዚህን ሰዎች በዚሁ መሰረት አላስገደድካቸውም ? “ ብዬ ስጠየቀው “ የንጉሳዊ ቤተሰቦችን ስልክ ቁረጥ ነው የምትለኝ ? “ ብሎ ሳቀ፡፡

በጣም ገረመኝ፡፡ ሚስተር ሊንድኮስት የወር ደሞዙ $5,000 ነው፡፡ ለቤት ክራይ $900 በወር ይከፈለዋል፡፡ ማርሴዲስ መኪና ከነሾፌሩ ከነነዳጁ ተሰጥቶታል ግን የቴሌፎን ክራይ እንኳዋን መሰብሰብ አልቻለም፡፡ በስራው ከታላላቆቹ ኢትዮጵያውያን ሹማምንቶች ለመወዳጀት እንጂ አላፊነቱን ለማስወረድ አልሞከረም፡፡ ከዚህም በቀር ከአገሩ ከስዊድን ስለቴሌኮሚኒኬሽን ምንም እውቀት የሌላቸውን ሰዎች በከፍተኛ ደሞዝ እየቀጠረ ሲያስመጣ ማንም ተቆጣጣሪ አልነበረውም፡፡ ስለዚህ የተሌኮሚኒኬሽን መሥሪያ ቤት “በኢትዮጵያ የስዊድን ኮሎኒ” ይባል ነበር፡፡ በዚያ ለሚሠሩ የስዊድን ቤተ ሰዎች ከግል መኪና በቀር ልጆቻቸውን ከትምህርት ቤት የሚያያመላልስና “ፒክኒክ” ወይም ሽርሽር የሚወስድ ትልቅ “እስቴሽንዋገን” በቴሌኮሚኒኬሽን መሥሪያ ቤት ገንዘብ ተገዝቶ ከነሾፌሩ ተሰጥቶታል፡፡ ይህ ሁሉ መቸም ያለእግባብ መሆኑን የማያውቅ የለም፡፡ ማን ቢናገር! ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ሚሰተር ሊንድኮስን ያለልክ ይፈሩታል፡፡ በክፍሉ ለመጉዳት እንደኮሌኒያል ገዢ ፍጹም ስልጣን ነበረው፡፡

ይህን ሁሉ ጉድለት መርምሮ ውሳኔ የሚሰጥ ኮሚሲዮን እንዲሾሙ ጃንሆይን ለመጠየቅ አንድ ማመልከቻ አሰናድቼ ነበር፡፡ ግን ለእንደዚያ ያለው ነገር የሚመርጡዋቸው ሕግ ተምረናል እያሉ የሚያጭበረብሩትን እንደሆነ ተገነዘብሁ፡፡ መቸም ቢመረጡ ሚስተር ሊንድኩሰትን እንደሚደግፉ አያጠራጥርም ነበር፡፡ ስለዚህ ለጃንሆይ ያዘጋጀሁትን ማምልከቻ ቀድጄ ከእሳት ውስጥ ጨመርሁና በቀጥታ አላፊነቴ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ ብዬ ቆረጥሁ፡፡ ቀጥሎም ለቦርዱ አባሎች አሳቤን ካካፈልኩዋቸውና የነሱን ድጋፍ ካገኘሁ በሁዋላ ለሚስተር ሊንድኩስት የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፈሁ፡፡

የተወደዱ ሚስተር ሊንድኮስት

በተቀጠሩበት ኮንትራት የተመለከቱትን ግዴታዎች በማፍረስ የቴሌኮሚኒኬሽን መሥሪያ ቤት ጥቅም የሚያበላሽ አድራጎቶች መፈጸምዎን ካረጋገጡ በሁዋላ አገለግሎትዎ ዛሪ ማለቁን ላስታውቅዎ እፈቅዳለሁ፡፡

እንደጠበቅሁት በዚህ ምክንያት የተነሳው ጩሀት ከአዲስ አበባ እስከዋሽንግተን ማሰጋባት ጀመረ፡፡ አቶ ይልማ ድሬሳ ስልክ ደውለው “ ከዓለም ባንክ ጋር ስምምነት ስላለን ዋናውን አስተዳዳሪ አንተ ልታሰናብተው አትችልም “ አሉኝ፡፡ አዲስ አበባ ያለው የዓለም ባንክ እንደራሴ “ ሚስተር ሊንድኮስትን ካባረርክ ብድር አይሰጣችሁም” ብሎ አስፈራራኝ፡፡ ያም ሆነ ይህ እኔ በውሳኔ ላይ ለመጽናትና ሕጋዊነቱን ለማስረዳት ተደራጅቻለሁ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ወዲያው የቴሌፎናቸውን ኪራይ ወደአልከፈሉት መሳፍንትና መኩዋንንት ጉዳይ ተመልሼ እስከ 15 ቀን ድረስ ባይከፍሉ አገልግሎት እንደሚያቁዋርጥ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ጻፍሁ፡፡ ግን የልዑል አልጋ ወራሽ እንደራሴ ብቻ በተወሰነው ጊዜ እዳውን ሲከፍል የቀሩት ማስጠንቀቂያውን ከምንም አልቆጠሩትም ነበር፡፡

የተወሰነው ጊዜ ካለፈ በሁዋላ ቴሌፎናቸው እንዲቆረጥ አዘዝሁ፡፡ በዚያ ቀን የፖስታ ሚኒስቴርና የቴሌኮሚኒኬሽን መስሪያ ቤት የጩሀት ማእበል አነቃነቃቸው፡፡ በመጀመሪያ ጥሪ የደረሰኝ ከራስ ቢትወደድ መኮንን እንዳልካቸው ነው፡፡ በቶሎ ከቢሮዬ ድረስ እንድተመጣ አሉኘ፡፡ በዚያን ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስተርነታቸውን ለቀው የሴኔቱ ፕሬዚዳንት ሆነው ነበር፡፡

ከቢሮአቸው ስገባ ሰላም እንኳዋን አላሉኝም፡፡ አፋቸውን የከፈቱት እኔን ለመስደብ ብቻ ነበር፡፡ መቸም እየደጋገሙ ሊያስገነዝቡኝ የሚፈልጉት እርሳቸው ክብር የዘራቸው የሆነ የመኩዋንንት ተወላጅ እኔ የመጣሁበት የማይታወቅ የደሀ ልጅ መሆኔን ነው፡፡ “ ከአመድ ላይ ይነሱና ሰው ነን ይላሉ” የሚል ነበር ንግግራቸው፡፡ ፊታቸው አመድ አይናቸው ደም ለብሶ የእብድ መልክ ነበራቸው፡፡ የቱን ያህል እንደሚጠሉኝ አይቼ ገረመኝ፡፡ በበኩሌ ስድባቸውን ዝም ብዬ ለመስማት ራሴን ከመቆጣጠሬ በቀር መልስ ልሰጣቸው

አልሞከርሁም፡፡ ስድባቸውን እንደመአት አወረዱብኝና ሲበቃቸው “ በል አሁን ሂደህ ስልኩን ቀጥል” ብለው አሰናበቱኝ፡፡ይህ መቼም የሚቻል አልነበረም።፡

ከራስ ቢትውደድ መኮንን ዘንድ ስመለስ ከጸሐፊዬ መልእክት ተቀበልሁ፡፡ የመጣው ከልዑል ሳህለሥላሴ ዘንድ ነበር፡፡ እርሳቸው ከቤታቸው በፍጥነት ሊያዩኝ ይፈልጋሉ፡፡መቸም እምቢ ማለት አልችልም፡፡ ግን የተቀበሉኝ በሰላምና በአክብሮት ነበረ፡፡ ቢሆንም በጣም አዝነው እንደነበረ በገጻቸው ይነበባል፡፡በቴሌፎናቸው መቆረጥ ምክንያት የደረሰባቸውን ችግር እየነገሩኝ ሳለ በድንገት እንባ አነቃቸውና ያለቅሱ ጀመር፡፡ ያለልክ ደነገጥሁ፡፡ በምን እንደምተረጉመው አስቸገረኝ፡፡

በመጨረሻ እንባቸውን ጠራርገው በድርጎ የሚኖሩ መሆናቸውንና እዳቸውን የሚከፍሉበት ራሳቸው የሚያዙበት ገንዘብ አለመኖሩን ገልጠው ይህንን ለጃንሆይ እንዳመለክትላቸው ስለጠይቁኝ ነገር ተዘብራረቀብኝ፡፡ ባንድ በኩል አነጋገራቸው ያለጥርጥር ልቤን ነክቶታል፡፡በሌላው በኩል ደግሞ “ለለዑል ሳህለሥላሴ አማላ ጅሆኜ ለመቅረብ እኔ ማን ነኝ ?” ብዬ ራሴን ጠየቅሁ፡፡ በማናቸውም አኳውሃን ከዚያስፍራ ለመሸሽ እንጂ ለመቆየት ስላልፈለግሁ ልዑልነታቸው የጠየቁትን ሁሉ እሺ ብዬ ተሰናበትሁ፡፡

ከልኡልነታቸው ቤት ስመለስ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ከአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ስልክ ተደወለልኝ፡፡ በጉዳዩ አቤቱታ ደርሶአቸው ኑሮአል፡፡ ሰለቴሌኮሚኒኬሽን ሥራ አካሄድ በጠቅላላው አቋዋሜን እንዳሻሽል ምክር የሚመስል ትእዛዝ ከሰጡኝ በሁዋላ ነገሩን በሰፊው ለመርመር ጊዜ እስካገኙ ድረስ የማስታወቂያ ምክትል ሚኒስቴር የነበረውን የኣቶ አምደ ሚካኤል ደሳለኝን ስልክ በቶሎ እንድቀጥል አዘዙኝ፡፡ እኔ ግን ትእዛዙን ሰምቼ ዝም አልኩዋቸው፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት በተለየ ቻርተር የተቋዋቅዋመ ስለሆነ ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ከዝርዝር ጉዳይ እየገቡ ለማዘዝ ሕጋዊ መብት እንደሌላቸው ተገንዜቤአለሁ፡፡ስለዚህ አቶ አምደ ሚካኤል ከቢሮዬ መጥቶ በጉዳዩ እንደገና በአነጋገረኝ ጊዜ እዳውን ሳይከፍል ምንም ላደርግለት እንድማልችል አረጋግጥሁለት፡፡

አቶ አክሊሉን የኔን እምቢታ ሲሰሙ ያለልክ ተቆጡና በቴሌኮሚኒኬሽን የደረሰውን ሁኔታ በማጣመም ለጃንሆይ አቅርበው ከሥራዬ እንድወገድ ጠየቁ፡፡ መቸም በዚህ የሚደግፉቸው ብዙ ሰው ነበር፡፡

በማግስቱ ከቤተመንግስት ማልጄ እንድገኝ በግርማዊነታቸው የልፍኝ አስከልካይ አማካይነት የተነገረኝ፡፡ ወዳጆቼ በሙሉ አዝነው ነበር፡፡ በጠቅላላው ሰው ሁሉ ገምቶት እንደነበረው በመንግስት ሥራ ለመቆየት ያለኝ ጊዜ አንድ ቀን ብቻ ነበር፡፡ ተወቅሼ ወይም ተቀጥቼ የምሰናበትበትና መጨረሻውን ሰዓት ለመመልከት ከቤተ መንግስቱ ቅጥር ብዙ ሰዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰማቸው ደስታ መቼም ግልጽ ነበር በመካከላቸው አልፌ ወደ ቤተ መንግስቱ ስገባ አንደንዶቹ እየተጠቃቀሱ ይሳሳቁ አንደነበር በአጋጣሚ ተመልክቼአልሁ፡፡ ከጃንሆይ ዘንድ እንደቀረብሁ አቶ አክሊሉ ቀደም ብለው በኔ ላይ አቅርበውት የነበረውን ክስ ደግመው ተናገሩ፡፡እንደሳቸው አነጋገር የቴሌኮሚኒኬሽንን ዋና ዳይሪክተር ከሥራው ለማገድ በቂ ምክንያት የለንም፣ በመሥሪያ ቤቱ ትርምስ ፈጥሬአለሁ፣ የቴሌፎን አገልግሎት የሚያስፈልጋቸውን ሹማምንቶች ያለአግባብ ከልክያቸዋለሁ። እንደርሳቸው አስተሳሰብ ሥራው ስነ ሥርዓት ለማግኘት የሚችለው እኔ ከዚያ ሰነሳ ብቻ ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህን ሁሉ ምክንያት በማድረግ እኔን ከዚያ ለማስነሳት ጃንሆይን ጠየቁ፡፡

የመከላኪያ ጊዜ ሲሰጠኝ “የቴሌኮሚኒኬሽን መስሪያቢት ‘የስዊድን ኮሎኒ’ እየተባለ የአኢትዮጵያ ሕዝብ ህብት ለግል ተጠቃሚዎች ይባክን በነበረበት ጊዜ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለማስመርመርና አስፈላጊው እርማት እንደደረግ አንዲት ቀን እንኩዋን አስበውበት አያውቁም” ሰል ንግግሬን ጀመርሁ፡፡ “የኢትዮጵያ መሳፍንቶችና የመንገስቱ ታላላቅ ሹማምንቶች በነጻ የቴሌፎን አገልግሎት ሲጠቀሙ ‘በምን ምክንያት?’ ብለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠይቀው አያውቁም፡፡ በኢትዮጵያ ላሉ የስዊድን ተወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት የሚያመላልስና ወደ ሽረሽር የሚወስድ አንድ ትልቅ እስቴሽንዋገን ቤቴሌኮሚኒኬሽን ገንዘብ ተገዝቶ ከሾፌርና ከነዳጅ ጋር ሲስጥ ‘በምን ምክንያት ነው?’ ብለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሊጠይቁ አልፈቀዱም፡፡ ስለቴሌኮሚኒኬሽኑ ስራ አንዳች የቴክኒክ እውቀት የሌላቸው ሰዎች ከስዊድን አገር በከፍተኛ

ደሞዝ እየተቀጠሩ ሲመጡ ‘በምን ምክንያት?’ ብለው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠይቀው አያውቁም፡፡ እርሳቸውን ያሳሰባቸው ከ8 እስከ 9 አመት የአገልግሎት ባለመክፈላቸው ቴሌፎናቸው የተቆረጠባቸው ሹማምንቶች ችግር ነው ! “ ስል በበኩሌ የፈጽምሁት ሁሉ ሕጋዊና ትክክለኛ መሆኑን የሚይሳዩ ልዩ ልዩ ማስረጃዎች አቀረብሁ፡ ፡ በዚያ ጊዜ ጃንሆይ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዘወር ብለው “ብርሃኑን የምትወቅስበት የሚበቃ ምክንያት አናይም፡፡ ይልቁንስ የሱን ጥረት መደገፍ ነበረብህ” ብለው አስናበቱን፡፡

በዚያ ጊዜ አቶ ወርቁ ሀብተወልድ የተባለው የቴሌኮሚኒኬሽን ቦርድ አባል የተናገረው በፍጹም አይረሳኝም፡፡ “ብርሀኑ በመንግስት ሥራ ላይ ያለው ጊዜ ዛሬ ያልቃል” እየተብባለ በከተማ ውስጥ የተወራውን ሰምቶ ለኔ በማዘን ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋራ ያለኝን የክርክር ውጢት ለመስማት እንደሌሎች ሰዎች ሁሉ በቤተ መነግስቱ ቅጥር ገብ ይጠባበቅ ነበረ።ከጃንሆይ ጽሕፈት ቤት እየሳቅሁ ስወጣ አንገቴን አቅፎ ከሳመኝ በሁዋላ ወደ ጆሮዬ ተጠገቶ “ የአጼ ሀይለሥላሴ ጥፋት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ መንገሳቸው ብቻ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች አፄ ሀይለሥላሴ የኢትዮፕያን ሕዝብ ንቅዝ አደረጉት እያሉ ሲከሱዋቸው ሌሎች ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ አፄ ሀይለሥላሴን ንቅዝ አደረጋቸው ይላሉ፡፡ እንግዲህ ፍርዱ የአንባቢ ነው፡፡